# እግዚአብሔር ምስሌነ

ትርጓሜውም እግዚአብሔር
ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው ።
ይህንንም የተነበየው ከክርስቶስ
ልደት በፊት በ፰ኛው መቶ ዓመተ
ዓለም የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስ
ነው ። ትንቢቱም እንደሚከተ
ለው ይቀርባል ። እነሆ ድንግል
ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳ
ለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠ
ራዋለች ሲል ገልጾታል ። ትን
ቢተ ኢሳይያስ ም. ፯.፲፬ ።

ወንጌላዊው ማቴዎስም ይህን
ተከትሎ ስለ አማኑኤል ልደት
በጻፈው ወንጌል ወንድ ልጅም
ትወልዳለች እርሱ ሕዝቡን ከኃጢ
አታቸው ያድናቸዋል ስሙንም
ኢየሱስ ትለዋለች ሲል ለዮሴፍ
ካመለከተው በኋላ ሁኔታውን
በመቀጠል በነቢይ ከጌታ ዘንድ
እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ
ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማ
ኑኤል ትለዋለች የተባለው ይፈ
ጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል
ትርጓሜውም እግዚአብሔር
ከእኛ ጋር የሚል ነው ። የማቴዎስ
ወንጌል ም.፩ ፳፩ ፳፫

በዚህም አባባል ከላይ እንደተገ
ለጸው አማኑኤል ማለት እግዚአ
ብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት
ስለሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
አማኑኤል ከድንግል ማርያም
በሥጋ ስለተገለጸ ሁል ጊዜ ከእኛ
ጋር ይኖራል ማለት ነው እነዚህ
ከላይ የተጠቀሱት ለጌታችን የክ
ብር ስሞቹ በመሆናቸው በሕዝብ
ዘንድ የታወቁ ናቸው በተጨማ
ሪም አማኑኤል ማለት ቃል ሥጋ
ሆነ ማለት ነው ።

ወንጌላዊው ሉቃስም በም.፪
፲-፲፬ እንደጻፈው ሕፃኑ አማኑ
ኤል በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ
መንጋቸውን የሚጠብቁ እረኞ
ችና መላእክት አንድ ሆነው ክብር
ለእግዚአብሔር በአርያም ሰላ
ምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ
ይሁን እያሉ የልደቱን በዓል በደ
ስታ አክብረውታል ብሏል ።

እያንዳንዳችንም ይህን አርአያ
ተከትለን ፣ የልደቱን በዓል በየዓ
መቱ ማክበር ይገባናል አንዳንድ
ሊቃውንት በአራተኛው ዓመተ
በዘመነ ዮሐንስ አማኑኤል ማክሰ
ኞና ሐሙስ ጾሙ ቀን የዋለ እንደ
ሆነ መግደፍ ይገባል በበኋላው
አርብ ግን መጾም አለባቸው ሲሉ
ሌሎች ሊቃውንት ደግሞ ጥንተ
ልደቱ ስለሆነ የአማኑኤል ዕለት
ተጾም ረቡዕና አርብ መብላት
እንጂ መጾም የለባቸውም ሲሉ
አንዳንዶቹ ደግሞ ሁለቱም መብ
ላት እንጂ መጾም የለባቸውም
እያሉ የልደቱን በዓል ሕዝቡ በደ
ስታና በሰላም እንዳያከብረው ሲለ
ያዩትና ሲከፋፍሉት ኖረዋል ።
ይህን የመሰለው መለያየትም የተ
ፈጠረው በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ
መንግሥት ከውጭ የመጡ የባዕ
ዳን ምሁራን እንክርዳድ የሆነውን
ትምህርታቸውን በሰንደው ላይ
ስለዘሩበት ነው በዚህ አኳኋን
መንግሥት ከሕዝብ ሕዝብም
ከመንግሥት ጋር ተለያየ ግጭ

ታህሣሥ ፳፰ ቀን የአማኑኤል ዕለት ተገድፎ በማግሥቱ በ፳፱ መጾም አለበት ሲል ሌላው ደግሞ ሀያ ስምንትም ሀያ ዘጠኝም መበላት አለበት በማለት ተከፋፈለ በዚህ ምክንያት አያሌ ሊቃውንትና ካህናት ተገደሉ ተሰደዱ ምእመናንም እርስ በእርሳቸው ተከፋፈሉ ይህም ጭቅጭቅ ሳይበርድ እስከ ዘመናችን እንደደረሰ ሁላችንም የምናውቀው ነገር ነው እንዲህ ያለውም ጭቅጭቅ በእኛ አገር ብቻ ሳይሆን እህቶቻችን በሆኑት በኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናትም ሊቃውንቱንና እማኞችን ለብዙ ጊዜ ሲያጨቃጭቅ ቆይቷል ይባላል በመጨረሻም ጭቅጭቅ አልበርድ ስላለ የግብፅ ሲኖዶስ በየአራት ዓመቱ ታኅሣሥ ፳፰ እና ታኅሣሥ ፳፱ እንዚህ ሁለቱ ቀኖች መጾም ሳይሆን ጥሉላት ሊበሉባቸውና የደስታ ቀን ሆነው ሊውሉ ይገባቸዋል ሲሉ በመወሰን ጭቅጭቅ ሊበርድ ችሏል ።

በሀገራችን ግን ጭቅጭቅ ውስጥ ውስጡን ከመሄድ በቀር በተግባር ሳይገለፅ ቆይቶ ነበር በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ግብፃዊው ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ እንዳንድ ሊቃውንትንና ትምህርት ያነሳቸውን መሳፍንት ወደ ቤታቸው እየጠሩ ማግባባት ጀመሩ በመጨረሻም ለዳግማዊ ምኒልክ ይህ የልደት በዓል በየአራት ዓመቱ ከሚያጨቃጭቅ ታህሣሥ ፳፰ እና ታኅሣሥ ፳፱ ቀን የግብፅ ሲኖዶስ እንደወሰነው ቢበላ ይሻላል የሚል ሃሳብ አቀረቡ ዳግማዊ ምኒልክም ነገሩ እውነት ስለ መሰላቸው የታወቁት ሊቃውንትና መሳፍንት አጥንተው እንዲያቀርቡ ወሰኑ ከአጥኚዎችም መካከል ፩ኛ ራስ መኮንን ፪ኛ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ፫ኛ ራስ ዳርጌ ሲሆኑ ከሊቃውንቱ መካከል ደግሞ ፩ኛ እጨጌ ገ/ሥላሴ ፪ኛ አለቃ ገብረሃና ፫ኛ መምህር አካለ ወልድ ነበሩ እቴጌ ጣይቱም ሰውን የማግባባትና ተናግሮ የማሳመን እድል ስለነበራቸው ሕዝብንና መንግሥትን የሚለያይ ሊቃውንትንም ሲያጨቃጭቅ የሚኖር እንዲህ ያለ መጥፎ ነገር ይጠና ማለትም በመጀመሪያ ጊዜ ፍቅርንና ታማኝነትን ከሕዝቡ ዘንድ የሚያሳጣ ነው ብለው ስለነገሩዋቸው ጥናቱ እንዲቀር ተደረገ ቀጥለውም እቴጌ ጣይቱ አቡነ ማቴዎስን አስጠርተው እርስዎን ያመጣንዎት ክህነት እንዲሰጡ እንጂ ሀገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን እንዲከፋፍሉ አይደለም ። በግብፅ ተወስኗል ስለሚሉት ግብፅ ሲሄዱ እዚያው ይፈጽሙት ሲሉ ገሠጿቸው ጳጳሱም ስለደነገጡ ነገሩን እርግፍ አድርገው ተውት ነገሩም እንደ በረዶ ቀዝቅዞ ቀረ ።

ነገሩ በዚህ ላይ እንዳለ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊነት ቢኖራትም ለ፩ሺ፮፻ ዓመታት ያህል የራሷ የሆነ ሲኖዶስ ሳታቋቁም ቆይታለች በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ለሁለት ጊዜ የሲኖዶስ ውሳኔ ተወስኖ ተብሎ ቢነገርም ከእስክንድርያ ተወስና የተላከ እንጂ ኢትዮጵያ በሚገኙው መንበረ ጵጵስና አልነበረም ከሁለቱ መካከል አንደኛው ውሳኔ ሕዝብንና ቤተ ክርስቲያንን የሚያለያይ በቤተ ክርስቲያን መካከል ሰላምንና ፍቅርን የሚያሳጣ ውሳኔ ነበር ይኸውም ከላይ እንደተጠቀሰው ታህሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ.ም በዘመነ የሐንስ አማኑኤል ሐሙስ ቀን ውሎ ነበር በማግሥቱ አርብ ቀን ጥንቱ ልደቱ የነበረው ባለ እግዚአብሔር አርብ ቀን ውሎ ስለነበር ሐሙስም ዓርብም ይበላ ሲል የግብፅ ሲኖዶስ አዟል በማለት ግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ቴርሎስ አዘዙ ደብዳቤም ወደየገዳማቱና ወደየአድባራቱ እንዲተላለፍ አደረጉ ይህንንም የኃይለሥላሴ መንግሥት ስለደገፈው እና በየግዛቱ ያሉትን ገዢዎች ግብር እንዲያበሉ በደብዳቤም በስልክም አስተላለፈ ሕዝቡና ካህናቱ ግን አንድ ወገን ሆነው ዓርብ ይጾማል እንጂ አይበላም ሲሉ ታላቅ ተቃውሞ አነሡ ። እንዳንድ ያወገዙ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች ታሰሩ ከእነዚህም መካከል ከእልቅናቸው የተሻሩ ነበሩ ዓርብን ሲጾሙና ሲያጾሙ የዋሉት ምሁራን በመሾምና በመሸለም ፈንታ ፀጋና ቅባት ናቸው የሚል መጥፎ ስም ተሰጣቸው ሲበሉና ሲያስበሉ የዋሉት ግን እውነተኛ የኦርቶዶክስ እማኞች ናቸው የሚል ስም ተሰጥቷቸው ነበር በዚህም መጥፎ ድርጊት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ሰላምና ፍቅር ሰፍቶ ጥልና ጭቅጭቅ ሰፍኖ ታላቅ መሰቃየት ተፈጥሮ ነበር ።

በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ በካህናትና በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት የነበራቸው የመካነ ኢየሱስ መነኩሴ አባ ዘገየ አማኑኤል የእመቤታችን በዓል እንጂ እራሱን የቻለ በዓል አይደለም በመሆኑም በየአራት ዓመቱ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን እና በሌሎችም ዓመታት ገሀድ ሆኖ ከመጾም በቀር የመግደፊያ በዓል ሊሆን አይገባውም ስለዚህም መረጃ የሚሆነን በጎንደር

ሀ/ስብከት በእስቴ ወረዳ በቂት አቡነ አረጋዊና በመሀልጌ ዕዮን በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ከግራኝ በፊት የተጻፉት ስንክሳሮች ለእሙ ኮነ እይሉም ያሬድም በድጓው ለሌሎቹ ለእሙ ኮነ ሲጽፍ ለአማኑኤል ግን ለእሙ ኮነ አልጻፈም ሐዋርያትም በዲዲስቅልያ ፻፶፲፮ ሲታውን ትም በፍትሐ ነገሥት በጥንተ ልደቱ ታህሣሥ ፳፱ ቀን ይገድፍ እሉ እንጂ ታህሣሥ ፳፰ ቀን የአማኑኤል ዕለት ይገደፍ የሚል ጽሑፍ አልጻፉም። አላስተማሩም ይህንንም በማድረጋቸው ሌላው ቀርቶ ይወዳቸው የነበረው የመካነ ኢየሱስ ሕዝብ እንኳ ፍቅሩን ቀንሰባቸው የበተኑትም ጽሑፍ ዛሬም በእያንዳንዱ ሰው እጅ ይገኛል ይህም ጭቅጭቅ ሳይበርድ እስከ ማይጨው ጦርነት ድረስ ቆየ ሕዝቡም በዚህ አቋም ስለነበር በጦርነቱ ጊዜ ጥቂቱ ሲቀር አብዛኛው ግን ወደኋላ አፈገፈገ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ድል ሆነው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ በየመንገዱ ታላቅ ጦርነት ገጠማቸው ይኸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ እምነቱንና ባህሉን የሚነካበትን ስለማይወድ በንጉሡ ቂም በመያዙ ነው ። ይህ ሁሉ ተቃውሞ የደረሰባቸው በዚህ ምክንያት እንደሆነ አንዳንድ ሰዎች ይነገራል ።

እንደገና ደግሞ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም በዓለ እግዚአብሔር አርብ ቀን ስለዋለ አብዛኛው ይጾም ሲል ጥቂቱ ደግሞ መበላት አለበት የሚል ጭቅጭቅ ተነሥቶ እንደነበር ይታወሳል ይህንኑ ጭቅጭቅ ለማብረድ ሲባል በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም በዘመነ ዮሐንስ አማኑኤል ታህሣሥ ፳፰ ቀን ማክሰኞ ቀን ስለዋለ ማክሰኞ እንዲበላና ረቡዕ ታህሣሥ ፳፱ እንዲጾም በመጀመሪያው ፓትርያርክ በአቡነ ባስልዮስ ሰብሳቢነት የጳጳሳት ስብሰባ ተደርጐ ነበር ። የተወሰነውም ውሳኔ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ ተላልፎ ነበር። ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ የነበረው መንግሥት የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደርና የሃይማኖት ጠባቂ እኔ ስሆን እኔን ሳያስፈቅድ ሲኖዶስ ለምን ወሰነ በማለት ውሳኔውን ተቃወመ ቀጥሎም ሶስት ሰዎችን ልኮ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተዘዋወሩ ሌሊት ደወል እንዲያስደውሉ ጧት ተቀድሶ እንዲበላና የሲኖዶስ ውሳኔ እንዲሻር አደረገ ያንጊዜ በአዲስ አበባ ከነበሩት ፶፪ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አራቱ አድባራት ፩ኛ ታዕካ ነገሥት በአታ ፪ኛ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ፤ ፫ኛ መንበረ ፀሐይ እንጦጦ ማርያም ፤ ፬ኛ ደብረአሚን ተክለሃይማኖት የሲኖዶስን ውሳኔ አክብረውና ጾም ውለው ሲቀድሱ የቀሩት ግን ጧት ቀድሰዋል በዚህም በሕዝብና በካህናት መካከል ጭቅጭቅ ተነስቶ በቤተ ክርስቲያንም ሰላምና ፍቅር ጠፍቶ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው መንግሥትም ይህን መጥፎ ድርጊት የተቃወሙትን የአራቱንም አድባራት አለቆች አስጠርቶ ውሎ እንዲበላ በማድረጋቸው ከባድ ወቀሳ ወቅሷቸው እንደነበር ከታሪክ ለመረዳት ይቻላል በአሁንም ሲኖዶስ ይኸው ውሳኔ እንዲከበር ትእዛዝ ተላልፏል ይሁን ሁሉ ለመዘርዘር የፈለግነው ጠንካራ የነበሩት የሃይማኖት አባቶቻችን እየታሰሩና እየተወቀሱ ያቆዩትን እምነትና ባህል እኛም አክብረን እንደናስከብረው ሕዝቡንም ይልተማሩ ሰዎች እንዳይከፋፈሉት በጋድር የሚከበረውም ታህሣሥ ፳፰ ፲፱፻፶፱ ዓ.ም የአማኑኤል ዕለት እንደሚገደፍና ታህሣሥ ፳፱ ቀን ደግሞ የሚጾም መሆኑን ቀደም ብለን ማስተማር ይገባናል ።

የዚህም ሐላፊነት ያለበት ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሆነ ትምህርት ያነሳቸው አንዳንድ የንስሐ አባቶች ቀሳውስት ታህሣሥ ፳፱ ቀን ይበላል አይጾምም እያሉ ሕዝቡን እንዳያሳስቱ ለማድረግ የየአድባራቱና የየገዳማቱ አስተዳዳሪዎችና መምህራን ለሚሰበሰበው ሕዝብ ትምህርት እንዲሰጡ እየሁሩም እንዲያስተምሩ ቢደረግ መካፋፈልና መለያየት ቀርቶ አማኞች አንድ ስለሚሆኑ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ሕዝቡ ሰላም ያገኛሉ ። ስለዚህ ትምህርት የማያሻሽለው ነገር ስለሌለ ሁላችንም ለማስተማር እንሠማራ እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር እንዲሆንልን ሕጉን በመጠበቅ ትእዛዙን በመፈጸም እንኑር ።

አለቃ ነቢየልዑል ዮሐንስ